

# የኢየሱስ መሞት

ወታደሮች ኢየሱስን ጎልጎታ ወይንም ቀራንዮ ተብሎ ወደሚጠራው ኮረብታ ወሰዱት።በእንጨት ላይ ሰቅለው ገደሉት። በመስቀል ላይ እንኳን ሆኖ የሰቀሉትን ይቅር አላቸው። ." “አባ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው።” ብሎ ፀለየ።

ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሆኖ እንኳን ብዙ ሰዎች እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ማወቅ ችለው ነበር። ከእነኝህ ሰዎች መካከልም አንደኛው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አብረው አጠገቡ ከተሰቀሉት ወንበዴዎች መካከል አንደኛው ነበር። ሌላኛው ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ ያመነውና ሁሉንም ነገር ሲመለከት የነበረው ሮማዊ ወታደር ነበር። የመሬት መንቀጥቀጡንና የሆነውን ነገር ሁሉ የተመለከተው ይህ ወታደር “ይህ እውነትም የእግዚአብሔር ልጅ ነው!” አለ።

ኢየሱስ ሲሞት የቤተ መቅደስ መጋረጃ  ከላይ እስከ ታች ድረስ ተቀደደ።  ይህ መጋረጃ ከመቀደዱ በፊት ሁለት የተለያዩ ክፍሎችን የሚለይ ነበር።  በአንደኛው ክፍል ውስጥ መግባት የሚችለው ሊቀ ካህናቱ ሲሆን በሌላኛው ክፍል ሌሎች ሰዎች መግባት ይችላሉ። ኢየሱስ ሲሞት ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔር ወዳለበት ድረስ በመሄድ ያለ ማንም ከልካይ እግዚአብሔርን ማምለክ ችለዋል። ኢየሱስ አሁን ሊቀ ካህናታችን ነው።

*ይህ ታሪክ የሚገኘው በማቴዎስ ወንጌል ምእራፍ 27፡ 32-65 እና በዮሐንስ ወንጌል በምዕራፍ 19 1-37 ባለው ክፍል ውስጥ ነው።*

http://gardenofpraise.com